# የአዘራር መመሪያ

1. **ማሳ መረጣ**
   - በትንሹ ሁለት 10ሜትር በ10ሜትር ስፋት ያለው መደብ የሚችል ማሳ ይምረጡ፤
   - ማሳው ወጥ መሆኑን ያረጋግጡ (በማሳው ውስጥ ትላልቅ ድንጋይ፣ ዛፍ፣ የምስጥ ኩይሳ አለመኖሩን ያረጋግጡ)




2. **የማሳ ዝግጅት**
   - ማሳውን ከዚህ ቀደም እንደሚያዘገጁት በአግባቡ ያዘጋጁት፤

3. **መደብ አወጣጥ**
   - በ10 ሜትር በ10 ሜትር የሆኑ ሁለት መደቦችን ይለኩ (1 ሜትር ከ1 እርምጃ ጋር ይመጣጠናል)፤
   - በአራቱም ማዕዘናት ችካል ቢቸከል ቦታውን በደንብ ለመለየት ይረዳል፤







4. **ፍግ**
   - ፍግ በማሳው ላይ የጨመሩ ወይም የሚጨምሩ  ከሆነ በሁለቱም መደቦች እኩል ፍግ መጨመሩን ያረጋግጡ፤

## 5. አዘራር




## 6. ማዳበሪያ አጠቃቀም

- ማዳበሪያ በመደብ ሁለት ላይ ብቻ ይጨምሩ፤
- በመስመሮች መሃል ያለው ርቀት 30 ወይም 40 ሳ.ሜ ቦይ ውስጥ 1 ቆርኪ ማዳበሪያ በየሁለት ተኩል ጫማ ርቀት ይጨምሩ፤
- ማዳበሪያውን አስቀድመው በቦይ ውስጥ በመጨመር ከአፈሩ ጋር ይቀላቅሉት፤




| የማዳበሪያው ዓይነት | መጠን | | |
|---|---|---|---|
| | (ለአንድ ሄክታር) | (ለ10ሜ በ10 ሜ) | (በመስመሮች መሃል ያለው ርቀት 30/40 ሳ.ሜ ቦይ ውስጥ) |
| ዳፕ/ ኤንፒኤስ | 100 ኪ.ግ | 250 ግራም | 1 ቆርኪ በየሁለት ተኩል ጫማ ርቀት |

## 7. ሰብል አሰባሰብ

- ሁለቱንም መደቦች ሳይደባለቁ በየመደባቸው ይጨዱ፤
- የመጀመሪያውን መደብ ወቅተው ሲጨርሱ የምርቱን መጠን በኪሎ ግራም ወይንም ባለው መለኪያ ለክተው መጠኑን ይመዝግቡ፤
- ሁለተኛውንም መደብ ወቅተው በተመሳሳይ መለኪያ የምርቱን መጠን ለክተው ይመዝግቡ፤

| ከመደብ 1 የተገኘ ምርት | ከመደብ 2 የተገኘ ምርት |
|---|---|
| | |